**28/09/2010**

# 90 ኤርትራውያን ስደተኛታት ሎሚ ምሸት ናብ ሳልሳይ ሃገር ክሰጋገሩ'ዮም፡፡

ነዘም ሎሚ ምሽት ናብ ሳልሳይ ሃገር ኣብ ምስግጋር ዝርከቡ ኤርትራውያን ስደተኛታት፣ ምምሕዳር ቤ/ጽሕፈት ጉዳይ ስደተኛታትን ካብ ስደት ተመለስትን ኢትዮጵያ ብክብ ዝበለ ናይ መፋነዊ ግብጃ ብዓርቢ መስከረም 24,2010 ኣብ ሰዓታት ድ/ቀትሪ ጌርሎም፡፡ ኣብ'ቲ ናይ መፋነዊ ስነ-ስርዓት ብምምሕዳር ቤ/ጽሕፈት ጉዳይ ስደተኛታትን ካብ ስደት ተመለስትን ኢትዮጵያ፡ ዝተዋህበ መግለጺ ኣብ ገጽ 2 ንመልከት፡፡ .........ገጽ 2.........!!

## ኣብ ሎሚ ዕለት መስከረም 28 ካብ ዝሰጋገሩ ምስሊ የሕዋት ብ'ኸፊል!!




መስከረም 13 ቀን 2003 ዓ.ም

## <u>በኢትዮጵያ ተጠልለው የሚገኙ ኤርትራዊያን ስደተኞች ወደ ሦስተኛ አገር ስለሚሄዱ አሸኛኘታቸውን አስመልክቶ</u>

## <u>የተሰጠ መግለጫ</u>

የኤርትራ መንግስት በዜጎቹ ላይ እያደረሰ ባለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት የሚሰደዱ የኤርትራውያን ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ የመጣ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በወር 1,900 በላይ ኤርትራዊያን ድንበር አቋርጠው እየመጡ ይገኛሉ:: ከእነዚህ ውስጥ 45% የኤርትራ ወታደሮች የነበሩ ናቸው::

የተለያዩ አገራት ለኤርትራዊያኑ ስደተኞች ዘላቂ መፍትሄ ከመስጠት አኳያ የሪሴትልመንት ዕድል በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ በዚህም አ.ኤ.አ  ከ2006 - 2009 ድረስ ብቻ 5,822 ኤርትራዊያን ወደ ተለያዩ አገሮች በሪሴትልመንት ሄደዋል::

በያዝነው የፈረንጆች 2010 ዓመት 3,100 ኤርትራዊያን ስደተኞች ወደ አሜሪካና ሌሎች አገሮች እንደሚሄዱ ይጠበቃል::

በዚሁ መሠረት በ2010 የፈረንጆች ዓመት ከተጀመረ ጀምሮ የዛሬዎቹን ጨምሮ 1,718 ኤርትራዊያን ስደተኞች በሪሴትልመንት ወደ ሦስተኛ አገር የተጓጓዙ ሲሆን፣ በዛሬው ዕለትም 90 ኤርትራዊያን ወደ አሜሪካ ተሸኝተዋል::

በአሁኑ ሰዓትም በአምስት መጠለያ ጣቢያዎች 53,767 ኤርትራውያን በትግራይ ክልል በሽመልባ፣ ማይዓይኒና አዲሐሩሽ፣ በአፋር ክልል በአሳኢታና በበራሕሌ እንዲሁም በተለያዩ ከተሞች ተጠልለው ይገኛሉ::

በዛሬው ዕለት የተሸኙትንም ስደተኞች በስደተኞች ጉዳይ አስተዳደር አሸኛኘት ተደርጎላቸው ወደ አሜሪካ የሄዱ ሲሆን ስደተኞቹን የማጓጓዝ ሥራ ከUNHCR  እና IOM ጋር በመተባበር እየተከናወነ ይገኛል::

**የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር**